አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

አንደኛ ዓመት ቁጥር ፲
አዲስ አበባ ፪ሺህ፩ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

First year – No. 10
ADDIS ABABA 2008


ማውጫ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርመሠረታዊ የሥራ ሒደት ለውጥን ለመተግበር የወጣ አዋጅ

Contents

ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT BUSINESS PROCESS RE-ENGINEERING IMPLEMENTATION PROCLAMATION

### አዋጅ ቁጥር ፲/፪ሺ፩
### መሠረታዊ የሥራ ሒደት ለውጥ ጥናትን ለመተግበር የወጣ አዋጅ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ እየተሠራባቸው ያሉ ሕጎችና የአሠራር ልምዶች በመሠረታዊ የሥራ ሒደት ለውጥ ጥናት የተገኙ አዳዲስ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን ለመተግበር የሚያስችሉ ሆነው በመገኘታቸው፣

በከተማው ውስጥ ተጠያቂነት የሚያስከትል ፣ ግልጽነትን የተላበሰ ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት ለኅብረተሰቡ በብቃት በመስጠት ከድህነት ለመውጣት የሚደረገውን ጥረት ለማሳካት መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናትን ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ ምቹ ሁኔታ መፍጠር በማስፈለጉ ፣

መሠረታዊ የሥራ ሒደት ጥናት ተግባራዊ ሲሆን የዲሞክራሲ ጽንሰ ሀሳቦችና የሕግ የበላይነትን መሠረት ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ፣

በጥናቱ የተደረሰባቸውን የአሠራርና የአደረጃጀት ማሻሻያዎችን በቋሚነት ተግባራዊ ለማድረግ በሥራ ላይ ያሉትን ሕጎች ከሙከራ ትግበራ በኋላ ማሻሻል በማስፈለጉ ፣

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፲፬/፩/ በተደነገገው መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል ፡፡

### PROCLAMATION No. 10/2008
### A PROCLAMATION TO IMPLEMENT THE BUSINESS PROCESS RE-ENGINEERING

**Whereas,** it is believed that the existing laws and practices hinder effective and efficient implementation of outcomes of the business process reengineering study in the governmental institutions of the City Government;

**Whereas,** the city Government desired to create fertile ground for effective implementation of the outcomes of the business process reengineering study and thereby to be successful in getting –rid off poverty by rendering accountable, transparent, fast and effective service to the public;

**Whereas,** it has become necessary to rely on the fundamental principles of democracy and rule of law in the course of implementing the business process reengineering;

**Whereas,** it is believed that permanent implementation of outcomes of the business process reengineering study demands amendment of the existing laws after pilot testing the process and structure;

**Now, therefore,** in accordance with Article 14(1) of the Revised Charter Proclamation No. 361/2003 of the Addis Ababa City Government, it is hereby Proclaimed as follows:


አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፳፬፻፵፭
Addis Negarit Gazeta P.O.Box 2445

ያንዱ ዋጋ
Unit price 3.35

## ክፍል አንድ
## አጠቃላይ

**፩. አጭር ርዕስ**

«ይህ አዋጅ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሠረታዊ የሥራ ሒደት ለውጥ ጥናት መተግበሪያ አዋጅ ቁጥር ፲/፪ሺ.ህ፩» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ፣

፩. «ምክር ቤት» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ነው ፡፡

፪. «ቻርተር» ማለት በ፲፱፻፺፭ ዓ.ም. ተሻሽሎ የወጣው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ እንደተሻሻለ/ ማለት ነው ፡፡

፫. «መሠረታዊ የሥራ ሒደት ለውጥ» ማለት በከተማው አስተዳደር መስሪያ ቤቶች ሥራን በሥራ ሒደት በማደራጀት ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል በተለያዩ የሥራ ሒደቶች ያካሄደውን ጥናት ውጤት የሚያመለክት ሐረግ ነው ፡፡

፬. «ካቢኔ» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ነው ፡፡

፭. «መሥሪያ ቤት» ማለት ቢሮ ፣ ፍርድ ቤት ፣ ኮሚሽን ፣ ጽህፈት ቤት ፣ ባለሥልጣን ፣ ተቋም ፣ ኤጀንሲ ወይም ማንኛውም ሌላ የከተማው አስተዳደር በአዋጅ ወይም በደንብ ያቋቋመው የሕዝብ አገልግሎት መስጫ ተቋም ነው፡፡

**፫. የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ አዋጅ ተፈፃሚ የሚሆነው መሠረታዊ የሥራ ሒደት ለውጥ ጥናትን በማጠናቀቅ ተግባራዊ በሚያደርጉና በሙሉም ሆነ በከፊል በከተማው አስተዳደር በጀት በሚተዳደሩ መሥሪያ ቤቶች ላይ ብቻ ይሆናል ፡፡

## ክፍል ሁለት
## ልዩ ልዩ ደንጋጌዎች

**፬. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

፩. የከተማው አስተዳደር ካቢኔ ለዚህ አዋጅ ሙሉ ተፈፃሚነት የሚያስፈልግ ደንብ ሊያወጣ ይችላል ፡፡

፪. የከተማው አስተዳደር የአቅም ግንባታ ቢሮ ይህን አዋጅ ተከትሎ የሚወጣውን ደንብ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል ፡፡

## Part One
## GENERAL

***1. Short Title***

This proclamation may be cited as the Business Process reengineering Implementation Proclamation No. 10/2008.

***2. Definition***

Unless expressed otherwise, in this proclamation:

1. "Council" shall mean the council of the City Government of Addis Ababa.
2. "Charter"" shall mean the Revised Charter of the City Government of Addis Ababa Proclamation No. 361/2003.
3. "Business Processing Reengineering" shall mean the outcomes of the study to organize the tasks of governmental institutions of the City Government in different job processes so that to enable them render effective and efficient public service.
4. "Cabinet" shall mean the executive council of the City Government of Addis Ababa.
5. "Governmental Institution" shall include Bureau, Court, Commission, Office, Authority, Institution, Agency or any other institution of the City Government established by proclamation or Regulations that renders service to the public.

***3. Scope of Application***

This proclamation shall be applicable only to the governmental institution that fully or partially run by government budget and those which implement the business process reengineering after accomplishing the phase of study.

## *Part Two*
## *Miscellaneous Provisions*

***4. Issuance of Regulations***

1. The Cabinet of the City Government may issue regulations for the proper implementation of this proclamation.
2. Capacity Building Bureau of the City Government may issue directives for the proper implementation of regulations to be issued in accordance with this proclamation.

፭. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

፩. በከተማው አስተዳደር ውስጥ የሚገኙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች መሠረታዊ የሥራ ሒደት ለውጥ ጥናት አጠናቀው ጥናቱ በከተማው አስተዳደር ምክር ቤት ወይም አግባብ ባለው አካል ፀድቆ ለውጡን ሲተገብሩ መሠረታዊ የሥራ ሒደት ለውጥ በተመለከቱ ጉዳዮች በሥራ ላይ ካሉ ማናቸውም አዋጅ ፤ ደንብ ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር ጋር ግጭት ቢፈጠር መሠረታዊ የሥራ ሒደት ለውጥን ለመተግበር የወጡ ሕጎች እና በጥናት የተገኘው አዲስ አሠራርና አደረጃጀት ተፈፃሚነት ይኖረዋል ።

፪. በዚህ አዋጅ ትግበራ ሒደት የሚፈፀሙ ማናቸውም የሕግ ድንጋጌ መተላለፍ አግባብነት ባለው ህግ መሠረት ታይቶ ውሳኔ የሚሰጥባቸው ይሆናሉ ።

፮. አዋጁ በሥራ ላይ የሚቆይበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በሥራ ላይ የሚቆየው በከተማው ምክር ቤት ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ ለሁለት ዓመት ብቻ ነው ።

፯. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከህዳር ፳፭ ቀን ፪ሺህ፩ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ህዳር ፳፭ ቀን ፪ሺህ፩ ዓ.ም.

ኩማ ደመቅሳ

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ

***5. Transitory Provision***

1. Any proclamation, regulation, directive or customary practice that does not go in conformity with laws and results of study of the Business process Reengineering shall not be applicable as regards matters covered therein.

2. Any Violation of laws during implementing this proclamation shall be adjudicated according to the existing laws.

***6. Duration .***

This proclamation shall remain in force only for two years as of its promulgation by the City Council.

***7. Effective Date***

This proclamation shall come into force as of the 4th day of December /2008.

**Done at Addis Ababa**

**4th Day of December, 2008**

**Kuma Demeksa**

**Mayor of Addis Ababa City**